የሰ/መ/ቁ. 47971

ሚያዝያ 05 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ሐጎስ ወልዱ

ሂሩት መለሰ

ብርሃኑ አመነው

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች፡-** ወ/ሮ ጅቦኒ ቱና - ቀረቡ

**ተጠሪ፡-** ወ/ሮ ብርቂ ኢርክታ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ ዋስትናን የሚመለከት ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኗ ተጠሪ ባሁኗ አመልካች እና በሌሎች ሁለት ግለሰሶች በስር ቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመሰረቱት ክስ ነው፡፡ የክሱ ይዘትም ባጭሩ አመልካች ሁለት ግለሰቦች (አቶ ፌደሳ ሽኑ እና አቶ ዘውዱ ሽመልስ) የተጠሪን መኖሪያ ቤት ሰብረው ገብተው ስምንት ላደና ገብስ ሰርቀዋል ተብለው በተጠረጠሩበት ጉዳይ በአካባቢ ሽማገሌዎች እና በአከባቢው ቡድን ፊት ቀርበው ፌደሳ ሽኑ ልጃቸው ስለሆነ፣ ዘውዱ ሽመልስ ባለቤታቸው ስለሆነ በተጠረጠሩበት ጉዳይ ሌባ እንዳልሆኑ ቦኩ ላይ ቀርበው ካልማሉ የተጠቁትን የእህል ግምት ገንዘብ እከፍላለሁ በማለት የዋስትና ግዴታ በግዴታዋ መሰረት የተጠረጠሩትን ሰዎች በቦኩ አቅርባ ካለማስማሏ በተጨማሪ ሰዎቹን ሸሽገው የእህሉን ግምት ሳያስከፍሉ የቀሩ መሆኑን ገልፀው የእህሉን ግምት እንዲከፍሉ ይወሰንላቸው ዘንድ ዳኝነት መጠየቃቸው የሚያሳይ ነው፡፡ የአሁኗ አመልካችም የገቡት ግዴታ አለመኖሩን ገልፀው ተከራክረዋል፡፡ ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ የተመለከተው የቀበሌ ማህበራዊ ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር በመመርመር የአሁኗን አመልካች ለክሱ ኃላፊ በማድረግ የእህሉን ግምት ብር 686.00(ስድስት መቶ ሰማንያ ስድስት ብር) እንዲከፍሉ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ አመልካች ባለመስማማት ይግባኛቸውን ለወረዳው ፍርድ ቤት የሰበር አቤቱታቸውን ደግሞ ለኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

አመልካች ነሐሴ 01 ቀን 2000 ዓ.ም በፃፉት ሁለት ገፅ የሰበር አቤቱታ በበታች ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ ከጉዳዩ ለማስረጃነት በቀረበው ሰነድ ላይ የተገለፀው የአመልካች ግዴታ ተጠርጣሪዎቹን ለማቅረብ ሆኖ እያለ ለተጠረጠሩበት እህል ግምት ክፍያ ትፈፅሚያለሽ መባሉ ከዋስትና ሕግ ድንጋጌዎች መንፈስ ውጪ ስለሆነ ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

አቤቱታቸውም ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ጥር 19 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገፅ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምረናል፡፡ እንደመረመርነውም አመልካች የገቡት የዋስትና ግዴታ አለ ወይስ የለም? የሚለው ነጥብ በጭብጥነት ሊመረመር የሚገባው ሆኖ አግኝተናል፡፡

በመሰረቱ ዋስትና በሕጉ ጥበቃ የሚያገኘው በፍ/ብ/ሕ/ቁጥር 1922 ድንጋጌ ስር የተመለከተውን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ነው፡፡ በዚህ ድንጋጌ መሰረት ዋስትና ግልፅ መሆን ያለበት ከመሆኑም በላይ ከተደረገው ውል ወሰን ለማለፍ የማይችል እና ለግዴታው ዋስ የሆነበት የገንዘቡ ልክ በዋስትናው ውል መገለፅ አለበት፡፡ ዋስትና ይህን ፎርማሊቲ ከማሟላቱም በተጨማሪ ለዋስትናው መሰረት የሆነው ዋናው ጉዳይም ሕጋዊ መሆን አለበት፡፡

በተያዘው ጉዳይ አመልካች ፈረሙ በተባሉት ሰነድ የዋስትና ገንዘቡ በግልፅ ተገልጾ የተቀመጠ ካለመሆኑም በላይ ለግዴታው መሰረት ነው የተባለው ዋናው ጉዳይም ተጠርጣሪዎች በሕግ አስገዳጅነት በሌለው ሁኔታ ቦኮ ሂደው እንዲምሉ የሚጠይቅ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በሕጉ አግባብ ጥበቃ የሚደረግለት የዋስትና ግዴታ አለ ለማለት የሚያስችል አይደለም፡፡ በመሆኑም የበታች ፍርድ ቤቶች በጉዳዩ ላይ የሰጡት ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## <u>ው ሣ ኔ</u>

1. በጀርማ ኮርጼሳ ቀ/ገ/ማ/ማህበራዊ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 050/2001 መጋቢት 02 ቀን 2001 ዓ.ም ተሰጥቶ በኤልፋታ ወረዳ ፍ/ቤት በመ/ቁ 09144 ሰኔ 02 ቀን 2001 ዓ.ም፣ በኦሮሚያ ክልል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 86060 ሐምሌ 15 ቀን 2001 ዓ.ም በትዕዛዝ የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽሯል፡፡
2. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሳራ የየራሳቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡
   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ራ/ታ